የኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት

# የጤና ፖሊሲ

# HEALTH POLICY

## OF THE

## TRANSITIONAL GOVERNMENT OF

## ETHIOPIA

መስከረም 1986

Sept. 1993

## ማ ው ጫ

## CONTENT

ገጽ
Page


1. መግቢያ .......................................................... 1

2. የፖሊሲው አጠቃላይ አቅጣጫዎች ...................... 5

3. ፖሊሲው ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ............. 7

4. አጠቃላይ ሥልቶች ............................................. 9

5. PREAMBLE ....................................................... 21

6. GENERAL POLICY ............................................ 24

7. PRIORITIES OF THE POLICY ........................... 26

8. GENERAL STRATEGIES .................................... 28

# የኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት
## የጤና ፖሊሲ

### መ ግ ቢ ያ

ኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ያላት የተለያዩ ሕዝቦችና ባህል የሚንፀባረቁባት አገር ብትሆንም በማኅበራዊ: በኢኮኖሚና በፖለቲካ ዕድገት እንዲሁም በቴክኖሎጂ መዳበር ኋላቀር አገር ናት። በሕፃናትና የእናቶች ሞት: በተላላፊ በሽታዎችና በምግብ እጥረት አማካይነት በሚከሰቱ ሞትና ሕመም: እንዲሁም በአማካይ በሕይወት የመኖር ዕድሜ በመሳሰሉት ተቀባይነት ባገኙት የጤና መለኪያዎች መሠረት ኢትዮጵያ በዓለም ዝቅተኛ ሥፍራ ላይ ከሚገኙት አገሮች መካከል ትመደባለች። ባለፉት ቅርብ ዓመታት የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎችና የፖለቲካ አለመረጋጋት ምክንያት በሕዝቦችዋ ላይ ይህ ነው የማይባል መከራና ስቃይ ደርሷል። እንዲሁም አገሪቷ የሕዝብ ውክልና ያለውና ተጠሪነቱና አደራው በግልጽ የተብራራ ሕዝባዊ መንግሥት ከቶም ኖሯት አታውቅም።

እስከ 1950ዎቹ ዓመታት ድረስ አገሪቷ በይፋ የወጣ የጤና ፖሊሲ አልነበራትም። ከዚያ ወዲህ የጤናን ዕድገት በተመለከተ መሠረታዊ የጤና አገልግሎቶችን በአገሪቷ በተዘረጉ የጤና ማዕከላትና የጤና ጣቢያዎች ማለትም የመከላከልና የማዳን ሕክምናዎችን ጎን ለጎን ለማካሄድ አመለካከቶች ይታዩ ነበር። በንጉሠ ነገሥቱ አገዛዝ ማክተሚያ አካባቢ በዓለም የጤና ጥበቃ ድርጅት አነሳሽነት አጠቃላይ የጤና አገልግሎቶች

ፖሊሲ በሥራ ላይ ውሎ ነበር። ሆኖም በሥርዓት መውደቅ ምክንያት የፖሊሲው ውጤታማነት ሳይረጋገጥ ቀርቷል።

በ1970ዎቹ አጋማሽ ላይ ሥልጣን ላይ ወጥቶ የነበረው አምባገነን የደርግ መንግሥት ለይስሙላ ያህል በበሽታ መከላከልና መቆጣጠር ላይ ያተኮረ የጤና አገልግሎት ለማስፋፋት: ለገጠር አካባቢዎች ቅድሚያ ለመስጠት በራስ መተማመንና የማኅበረሰቡን ተሳትፎ በማጎልበት ላይ የተመረኮዘ የጤና ፖሊሲ አውጥቶ ነበር። ነገር ግን የነበረው ሥርዓት የሕዝብን ተሳትፎ የማይፈቅድና ሊፈቅድም የማይችል ስለነበረ ፖሊሲውን በተግባር ለመተርጎም ሳይቻል ቀርቷል። በተጨማሪም አብዛኛው የአገሪቷ ሀብት ሥርዓቱ በቆየበት ጊዜ በሙሉ ለጦርነት ማካሄጃ በመዋሉ በማንኛውም ዘርፍ ለልማት እንቅስቃሴዎች በቂ ገንዘብ ሊኖረው አልቻለም።

ስለዚህ ባለፉት ሁለቱ ሥርዓቶች ውስጥ በጤናም ሆነ በሌሎችም ዘርፎች በተገለፁት ዓላማዎችና በተጨባጭ በታዩት ክንዋኔዎች መካከል ግንኙነት አልነበረም። ከዚህም በተጨማሪ የጤና አስተዳደራዊ መዋቅር ለጤናው ዘርፍ ልማት መጓተት የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ምክንያቱም እንደሌሎቹ በማዕከላዊነት የተወጠሩ ቢሮክራሲዎች ሁሉ የጤና ዘርፍም ኃላፊነት የማይሰማው: ለራሱ ብቻ የቆመና ለለውጥ ደንታ ቢስ በመሆኑ ነበር።

ከዚህ በመነሳት የሽግግሩ መንግሥት የጤና ፖሊሲ የአገሪቷን ወቅታዊ የጤና ችግሮች ባህሪ: ስፋትና መሠረታዊ መንስዔዎችን በአንክሮ በመመርመርና ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉትን አዳዲስ የጤና ችግሮች በመገንዘብ የተቀረጸ ነው።

ፖሊሲውም የተመሠረተው በዲሞክራሲ እምነት ላይ በመሆኑ ከሱ የሚመነጩትን የሕዝብ መብትና ሥልጣን ግምት ውስጥ አስገብቷል። የብዙ ብሔር/ብሔረሰቦች አገር በሆነችው ኢትዮጵያ የሕዝብ መብቶችን ለማስከበር አግባብ ያለው ሥርዓተ-መንግሥትና ያልተማከለ አወቃቀር እንደሚያስፈልግ ግንዛቤ ተደርጓል። የአገሪቷ ዋና የአምራች ኃይል ለሆነውና ከሕዝቡ ከፍተኛውን ቁጥር ላካተተው እንዲሁም ጥቅሙና መብቱ እስካሁን ላልታየለት የገጠሩ ኅብረተሰብ ተገቢውን ትኩረት ይሰጣል። ጤንነት ማለትም የአካል: የአእምሮና የማኅበራዊ ደህንነት: ደስተኛ ኑሮ ለመኖርና ከፍተኛ ምርታማነትን ለመቀዳጀት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ተጨባጭ ግቦች ተተልመዋል። እነዚህ ግቦች ላይ ለመድረስ የአገር ውስጥና የውጭ ድጋፎችን በሰፊው ለመጠቀም አግባብ ያላቸው ዘዴዎችና አቅጣጫዎች ለመከተል ወስኗል። በተለይም የሕዝብ ንቁ ተሳትፎና የራስ አቅምን ማጎልበት ቁልፍ ሚና ስለሚጫወቱ እነዚህ ባህሎች እንዲስፋፉና እንዲዳብሩ የማኅበራዊና የፖለቲካ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ከዚህም በመነሳት መንግሥት ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል ጤና ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል።

የጤና ፖሊሲ የሕዝብ ዕድገትን: የምግብ አቅርቦትን: ተስማሚ የኑሮ ሁኔታዎችንና ሌሎችም ለጤና መሻሻል በጣም አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ከሚመለከቱ ፖሊሲዎች ተነጥሎ የሚታይ አይደለም። ስለዚህ የሕዝቡን አጠቃላይ ኑሮ ለማሻሻል መንግሥት በዘርፎች መካከል የሚኖረውን መደጋገፍ ለማጎልበት ቆርጦ ተነስቷል።

በአጠቃላይ የጤና አገልግሎት ዕድገት ለሰብዓዊነት ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት አስፈላጊ ከሆኑ ጥቅል ግባቶች አንዱ አካል ሆኖ መታየት አለበት። እንዲሁም ለሕዝብ ፍትሕና እኩልነት መጠበቂያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል።

ከዚህም በመነሳት የሽግግሩ መንግሥት የጤና ፖሊሲ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች ያቅፋል።

## የፖሊሲው አጠቃላይ አቅጣጫዎች

1. የጤና አገልግሎትን ሥርዓት ዲሞክራሲያዊና ከማዕከላዊነት የተላቀቀ ማድረግ:

2. በጤና እንክብካቤ የማሻሻያና መከላከያ ዘዴዎችን ማጎልበት:

3. ባለው ውሱን ሀብትና አቅም ለሁሉም የኅብረተሰቡ ክፍል ፍትሐዊና ተቀባይነት ባለው መንገድ የጤና አገልግሎት የሚያደርስ ሥርዓት መዘርጋትና ማስፋፋት:

4. በዘርፎች መካከል ያለውን የጋራ እንቅስቃሴ መደገፍና ማጠናከር:

5. በጤናው ዕድገት ውስጥ በአገር ደረጃ የራስን አቅም ለማጎልበት: የውስጥና የውጭ ዕርዳታዎችን ለማሰባሰብና ለመጠቀም የሚረዱ ተስማሚ አመለካከቶችንና ድርጊቶችን ማስፋፋት:

6. የጤና እንክብካቤውን ሁሉም የኅብረተሰቡ ክፍል እንዲጠቀምበት ማረጋገጥ:

7. ከጎረቤት አገሮችና እንዲሁም ከአህጉራዊና ከዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር ለጤና ዕድገት አስተዋጽኦ በሚያደርጉ እንቅስቃሴዎች ሁሉ መተባበር የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ለጤና ጠንቅ የሚሆኑ ነገሮችን አብሮ መቆጣጠር:

8. በተጠኑ ፍላጎቶች ላይ በመመሥረት ተገቢ አቅምንና ብቃትን ማነጽና ማጎልበት:

9. አቅም ያላቸውን እንደችሎታቸው ለማስከፈልና አቅም የሌላቸውን ደግሞ እገዛ በማድረግ ለማከም የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት ለኅብረተሰቡ የጤና አገልግሎት መስጠት:

10. በጤናው እንክብካቤ የግሉን ዘርፍና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ተሳትፎ ማስፋፋት:

## ፖሊሲው ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች

1. ጤንነትን መጠበቅ የግል ኃላፊነት መሆኑን የሚያሰርፁ ፅንሰ-ሀሳብና ድርጊቶችን ለማስፋፋት እንዲሁም ስለጤንነት የሚያስፈልገውን ግንዛቤ ለማጎልበት የመረጃ፣ የትምህርትና የመገናኛ መርሐ-ግብሮች ተገቢው ትኩረት እንዲያገኙ ይደረጋል።

2. የሚከተሉት የጤና እንቅስቃሴዎች ይበልጥ ትኩረት ይሰጣቸዋል።

   2.1. ወረርሽኝና ተላላፊ እንዲሁም ከምግብ ማነስና ከዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር፡

   2.2. የሠራተኞችን ጤንነትና ደህንነት ማራመድ፡

   2.3. የአካባቢ ደህንነትን ማጎልበት፡

   2.4. የጤናን ኢንፍራስትራክቸር መልሶ ማቋቋም፡

   2.5. ተስማሚ የጤና አገልግሎት አመራር ሥርዓትን መቅረጽ፡

3. ፈዋሽና የማገገም አገልግሎቶች የአእምሮ ጤንነትን ጨምሮ ተገቢው ድጋፍ ይሰጣቸዋል።

4. የባህል መድኃኒቶችን ጠቃሚ ጎን ለማጎልበት ተገቢው ትኩረት ይሰጣል። ከዚህም ጋር የተያያዙ ምርምሮች እንዲሁም ከዘመናዊ የሕክምና ዘዴዎች ጋር ቀስ በቀስ ለማቀናጀት የሚረዱ ዘዴዎች ይበረታታሉ።

5. ዋና ዋና የጤና ችግሮች ላይ ያተኮረ ተግባራዊ ምርምር ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጠዋል።

6. የአስፈላጊ መድኃኒቶች: የሕክምና ግባቶች መሣሪያዎችና አገልግሎቶች አቅርቦት ይጠናከራል።

7. በጤናው መስክ በቂና አግባብ ያለው የሰው ኃይልን ለማፍራት በግምባር ቀደምና በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠኑ በተለይም በኅብረተሰቡ ፍላጎት ያተኮሩና ለተግባር የተዘጋጁ የጤና ባለሙያዎችን ማሰልጠን።

8. ለሚከተሉት የኅብረተሰብ ክፍሎች የጤና አገልግሎት ፍላጎት ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

   8.1. ለቤተሰብ በተለይ ለሴቶችና ለሕፃናት:

   8.2. በግንባር ቀደምነት በማምረት ተግባር ላይ ለሚሳተፉ:

   8.3. እስከ ዛሬ ድረስ ተረስተው ለቆዩት ክልሎችና የኅብረተሰቡ ክፍሎች: ማለት ለአብዛኛው የገጠሩ ሕዝብ: ለከብት አርቢዎች: ለደሃ ከተሜዎችና አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሔረሰቦች:

   8.4. በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ለተጠቁ:

## አጠቃላይ ሥልቶች

1. ዋና ዋና የጤና ችግሮችን ለመለየት: የጤና እንቅስቃሴዎችን ለማቀድ: ለመተግበር: ለመቆጣጠርና ለመገምገም: በጀትን ለመመደብ: በሁሉም ደረጃዎች ጠንካራ የሕዝብ ውክልና ያለው የጤና ምክር ቤቶችና በታዕታይ ደረጃ ደግሞ የጤና ኮሚቴዎችን በማቋቋም የጤናው ሥርዓት ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን ማድረግ:

2. የክልሎችን ሚና በግልፅ በማስቀመጥ የጤና አገልግሎቶችን ማደራጀት: የአቅም ግንባታ: የዕቅድ መንደፍ: መተግበርና መቆጣጠር እንዲሁም አብዛኛውን ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን በማዛወር ያልተማከለ አሠራርን ዕውን ማድረግ:

3. የልዩ ልዩ ዘርፎች የእርስ በርስ ግንኙነትና መደጋገፍ በተለይ በሚከተሉት ላይ ያተኩራል።

   3.1. የሕዝብ ዕድገትን በአቅድ ለመምራት ለተሟላ የቤተሰብ ጤንነትና ምጣና የቤተሰብ ቁጥጥር ፅንሰ-ሀሳብ ማስተዋወቅ ተግባራዊ እንዲሆን መገፋፋት:

   3.2. አግባብ ያለው የምግብና የሥርዓተ ምግብ ፖሊሲ መቅረጽና መተግበር:

3.3. ለገጠርና ለከተማ ሕዝቦች ንፁህና በቂ የመጠጥ ውሃ የሚዳረስበትን መንገድ ማፋጠን:

3.4. የሰው: የቤት: የእርሻና የኢንዱስትሪ (ደረቅና ፈሳሽ) ቆሻሻዎች የሚወገዱበት ተስማሚ ዘዴዎችን ማዘጋጀት: እንዳግባቡም እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ዘዴ ማበረታታት:

3.5. የመኖሪያ ቤቶችንና የሥራ ሥፍራዎችን አሰራርና አያያዝ ጥራት የሚያሻሽሉ እርምጃዎችን ማጎልበት:

3.6. ለአካልና የአእምሮ ጉዳተኞች: የተጣሉና ሰብሳቢ አጥተው በመንገድ ለሚንከራተቱ ሕፃናትና ለአረጋውያን እንክብካቤ በኅብረተሰቡ ውስጥ በሚቋቋሙ አገልግሎቶች ማስፋፋት ተግባር መሳተፍ:

3.7. በፋብሪካዎችና በተቋሞች ውስጥ በሚቋቋሙ መዋለ ሕፃናት: የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎትና የሥርዓተ ምግብ ፕሮግራሞች ዝግጅትና ግንባታ መሳተፍ:

3.8. አደጋን በመቋቋም: በእርሻ: በትምህርት: በመገናኛ: በትራንስፖርት: የሥራ ዕድልን በማስፋፋትና ሌሎችም ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በማጎልበት ተሳትፎ ማድረግ:

3.9. የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ በምርት ሥፍራዎች ዝግጅቶችና አገልግሎቶች እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ መርዳት:

4. በመገናኛ ብዙኃን: አማካይነት በአጠቃላይና ለተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች አግባብ ያለው የጤና ትምህርትን መስጠት። የማኅበረሰብ: የሃይማኖትና የባህል መሪዎችን: የሙያ ማኅበራትን: ትምህርት ቤቶችንና ሌሎችም ማኅበራዊ ተቋሞችን በማሳተፍ እንዲጠናከር ማድረግ። የዚህም ዓላማ የሚከተሉትን ውጤቶች ለመቀዳጀት የሚያግዙ ይሆናሉ።

4.1. በሕዝቡ ዘንድ የግልን ጤና መጠበቅ ኃላፊነትና ልምድ እንዲሰርጽ ለማድረግና የአካባቢ ደህንነትን ለማረጋገጥ:

4.2. ጤናማ የኑሮ ዘዴዎችን ለማጎልበት ለግል ንጽሕናና ለጤናማ አካባቢ ትኩረት ለመስጠት የሚረዱ ግንዛቤዎችን ለማስጨበጥ:

4.3. ባመጋገብ የሚመጡና ተራ ተላላፊ በሽታዎችን የማወቅና የመከላከል ግንዛቤን ለማሳደግ:

4.4. የማኅበረሰቡን ጤና ማሻሻል በተመለከተ ሕዝባዊ ተሳትፎን ለማሳደግ:

4.5. ከባህላዊ ልማዶች ጎጂዎችን በመለየትና በማስቀረት ጠቃሚ የሆኑትን ለማጎልበት:

4.6. ከማጨስ: ከጠጭነት: ከዕፅ ሱሰኝነት: ኃላፊንት ከጎደለው ወሲባዊና ጎጂ ባህርያት ለመጠንቀቅ:

4.7. ሕዝቡ በተገቢው መንገድ በመድኃኒቶች እንዲገለገል ግንዛቤ ለመፍጠር:

5. የጤና እንክብካቤ ማጎልበቻና የበሽታ መከላከያ እንቅስቃሴዎች በሚከተሉት ላይ ያተኩራሉ።

5.1. አግባብ ያላቸው አጠቃላይና የተለያዩ እርምጃዎችን በመጠቀም የተለመዱ የወረርሽኝና በምግብ የሚመጡ በሽታዎችን መቆጣጠር:

5.2. ከምቾትና ከዕድሜ መግፋት ጋር የሚመጡ በሽታዎች እንደ ዋና የጤና ችግሮች ብቅ እንዳይሉ መከላከል:

5.3. አካባቢ በአስጊ ንጥረ ፍሳሽ እንዳይበከል መከላከል:

6. የሠለጠነ የሰው ኃይል ሥምሪት በሚመለከት በሚከተሉት ላይ ትኩረት ይደረጋል።

6.1. በጤና እንክብካቤ የቡድን አሠራርን የሚያዳብር ሥርዓት መቀየስ:

6.2. የሕብረተሰቡ አካል ሆነው ልዩ ተልኮና ብቃት ያላቸው ግምባር ቀደምና የመካከለኛ ደረጃ የጤና ሠራተኞችን ማሠልጠን። እነዚህም በየክልሉና በየአካባቢው እንዲመለመሉና እንዲሰለጥኑ ማድረግ:

6.3. አሠልጣኞችን: አስተዳዳሪዎችንና ድጋፍ ሰጪ ኃይሎችን ከጤና አገልግሎቱ ዓላማዎች አቅጣጫ ማሠልጠን:

6.4. በጤናው ዘርፍ በሁሉም ደረጃዎች ለሚገኙ የጤና ሠራተኞች ተገቢና ተከታታይ ትምህርት ማዘጋጀት:

6.5. በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ ሠራተኞች የሚስብ አከፋፈል ማትግያና የሙያ መስክ መዋቅር መዘርጋት:

7. የመድኃኒቶች: የሕክምና መሣሪያዎችና መገልገያዎች አቅርቦትን አስተማማኝ ለማድረግ:

7.1. በጤናው አገልግሎት ሥርዓት በሁሉም ደረጃዎች የሚያስፈልጉና ደረጃቸውን የጠበቁ መድኃኒቶችን: መሣሪያዎችን ዝርዝር ማዘጋጀትና ይህንንም ዝርዝር በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ:

7.2. መድኃኒቶችን: የከትባት መገልገያዎችን: የሕክምና ቁሳቁሶችንና መሣሪያዎችን በአገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለማጎልበት: በመፈብረክ: ምርምር በማካሄድና በማልማት ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች ተገቢውን ድጋፍ መስጠት:

7.3. የምርቶች ግዢ: ሥርጭት: ክምችትና አጠቃቀም እንዲሻሻል ደረጃውን የጠበቀና ቀልጣፋ ሥርዓት መፍጠር:

7.4. የምርቶችን ደህንነትና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ የጥራት ደረጃ ቁጥጥር አቅምን ማጎልበት:

7.5. የመሣሪያዎች ጥገናና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ማስፋፋት:

8. የአገር ባህል መድኃኒቶች በሚከተሉት መንገዶች ተገቢውን ትኩረት ያገኛሉ።

8.1. ጠቃሚ ጎናቸውን በመለየት አጠቃቀማቸውን ማበረታታት፡

8.2. በዚህ መስክ የሚካሄደውን ምርምር ማስተባበርና ማበረታታት። እንዲሁም ከዘመናዊ ሕክምና ጋር ሊኖራቸው የሚገባውን ግንኙነት ማጠናከር፡

8.3. አገልግሎት አሰጣጣቸውን በተመለከተ ተገቢ የሆ ነ ደንብና የምዝገባ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፡

9. የጤና ምርምር በሚከተሉት ላይ ትኩረት ያደርጋል።

9.1. በጤናው ዘርፍ የምርምር ትኩረት መስኮችን በመለየት፡

9.2. በዋና ዋና የጤና ችግሮችና የጤና አገልግሎት ሥርዓቶች ተግባራዊ ምርምርን በማስፋፋት፡

9.3. ኃላፊነቱ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ጋር በመደጋገፍ የብሔራዊ ተቋሞችንና ሳይንቲስቶችን የምርምር ማካሄድ አቅም በማጠናከር፡

9.4. በምርምር ተግባር ጥብቅ ሥነ ምግባር መኖሩንና መከተሉን በማረጋገጥ፡

10. የቤተሰብ ጤና አገልግሎቶች በሚከተሉት መሠረት ይጎለብታሉ።

10.1. በቂ የእናቶች ጤና እንክብካቤና ለአደገኛ እርግዝናዎች አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ:

10.2. የእናቶችን: የሕፃናትንና የቤተሰብን የጤና ደረጃ የተሟላ ለማድረግ የቤተሰብ ምጣኔን ማስፋፋት:

10.3. ተገቢው የወላዶች አመጋገብ መርሆ እንዲለመድ ማድረግ:

10.4. የጡት ማጥባት ልምድን ማጠናከር: በተጨማሪም በተመጣጣኝ ዋጋ የሕፃናት ምግቦች በቤት ውስጥ እንዲመረቱና እንዲዘጋጁ ማበረታታት:

10.5. የክትባት አገልግሎቶችን ማስፋፋት: ማጠናከር: አቅርቦታቸውንና አጠቃቀማቸውን ከፍ ማድረግ:

10.6. የተለመዱ የሕፃናት በሽታዎችን በተለይ የተቅማጥና የመተንፈሻ አካላት ተላላፊ በሽታዎችን ለመቆጣጠር ባሉት የጤና መገልገያዎች በወቅቱ መጠቀምን ማበረታታት:

10.7. የወጣቶች ልዩ የጤና ችግሮችና ከዕድሜአቸው ጋር የተያያዙ የጤና ፍላጎቶች ላይ ትኩረት ማድረግ:

10.8. በቤተሰብ ጤና አጠባበቅ የአባቶችን ተሳትፎ ማበረታታት:

10.9. ከአገር ባህል ልማዶች ጎጂዎችን በመለየትና በማስቀረት ጠቃሚ የሆኑትን ማጎልበት:

11. የጤና አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ወደሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ሥርዓት በሚከተሉት መንገዶች ይጎለብታል።

11.1. የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን አጠቃቀም በሁሉም ደረጃዎች በማሳደግ:

11.2. የጤና እንክብካቤ አገልግሎትን እንደአስፈላጊነቱ በቅርብ የማግኘት ሁኔታን በማሻሻል:

11.3. በሁሉም ደረጃ ተከታታይና ጥራት ያለው ሕክምና መሰጠቱን በማረጋገጥ:

11.4. የጤና ተገልጋዮችን ወጪና የሰጪዎችን ዋጋ ሚዛናዊ በማድረግ: በሁሉም ደረጃ የጤና ድርጅቶች አጠቃቀምን በማሳደግ:

11.5. በሕክምናው ሥርዓት ውስጥ የርስ በርስ ግንኙነትን በማጠናከር:

12. ለጤናው እንክብካቤ የምርመራና ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች በሚከተሉት አኳኋን ይጎለብታሉ።

12.1. የጤና እንክብካቤን ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት በማጠናከር:

12.2. ፈጣን ምርመራና ሕክምና እንዲገኝ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር:

12.3. ለተከታታይ የጤና እንክብካቤ ተገቢውን አመራር በመስጠት:

13. የጤና አገልግሎትንና አመራርን ለማሻሻል የመረጃ ሥርዓት በሚከተለው መንገድ ይደራጃል።

13.1. ሥርዓቱን ለውሳኔ አሰጣጥ፣ ለዕቅድ መንደፍ፣ ለክትትልና ለግምገማ ምቹና ብቁ ማድረግ፣

13.2. በሁሉም ደረጃዎች የመረጃን አጠቃቀም ማሳደግ፣

13.3. በክልሎችና በማዕከል የመረጃ ማሰባሰቢያና ማከማቻዎችን ማስፋፋት፣

14. ጤና ነክ ሕጎች በሚከተሉት አኳኋን ይሻሻላሉ።

14.1. በሥራ ላይ ያሉትን ጤና ነክ ሕጎችና ደንቦች ወቅታዊ ማድረግ፣

14.2. አዲሱን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግና አዳዲስ የጤና ጉዳዮችን ለማስተናገድ ተጨማሪ ሕጎችና ደንቦችን ማውጣት፣

14.3. የጤና ሕጎችና ደንቦችን ለመተግበር ያሠራር ሥልቶችን ማጠናከር፣

15. የጤና አገልግሎት ድርጅቶች በሚከተለው ሥርዓት በአግባቡ ይደራጃሉ።

15.1. በተለያዩ የጤና ክፍሎች የሚገኙ የሰው ኃይል: ቋሚ አገልግሎቶችና የአሠራር ሂደት ሥርዓቶች ደረጃ የጠበቁና የተከተሉ ማድረግ:

15.2. በጤናው ችግሮች: በሕዝብ መጠን: በትራንስፖርት ምቹነት: ከሚቀጥለው የጤና ጣቢያ ባለው ርቀት: በመገናኛና በወደፊት የልማት ዕቅድ ላይ በመመሥረት የበሽተኞች ማስተናገጃ ድርጅቶችን አቀማመጥና የማስተላለፍ ሥርዓቶችን መለየትና መወሰን:

15.3. አግባብ ያለው የሥራ ፈቃድ በመስጠት የግል የሕክምና ድርጅቶችንና የባለሙያዎች ሥርጭትን ሥርዓት ማስያዝ:

16. የጤናን ሥርዓት አስተዳደርና አመራር ለማጠናከርና ይበልጥ ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ:

16.1. ከወቅቱ የዲሞክራሲና ያልተማከለ የአስተዳደር ፖሊሲ አንፃር በውሳኔ አሠጣጥና አመራር በሁሉም ደረጃዎች አስተዳደሩንና አመራሩን እንደገና ማዋቀርና ማደራጀት:

16.2. በሥራ ፀባያቸው ግንኙነት ያላቸውን መምሪያዎችና አገልግሎቶችን ማዋሃድና የሰውና የቁሳቁስ ኃይሎች አጠቃቀምን በአግባቡ በሥራ ላይ ማዋል:

16.3. ያገልግሎት ተከታታይነትን ለማረጋገጥ በዋናው መሥሪያ ቤት ቋሚ አስተዳዳሪ የሚሰየምበትን መንገድ ማጥናት:

16.4. የብሔራዊ ሆስፒታሎችን: ተቋሞችንና ድርጅቶችን የሚያስተዳድሩ የአመራር ቦርዶች ማቋቋም:

16.5. የጤና ተቋሞች አገልግሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ከገቢያቸው የተወሰነውን እንዲጠቀሙበት መፍቀድ:

16.6. በሁሉም ደረጃዎች በአግባቡ የሠለጠኑና የሥራ ፍላጎት ያላቸው ሠራተኞች መመደባቸውን ማረጋገጥ:

17. ለጤናው አገልግሎት የሚውል ገንዘብ ከመንግሥት: ከግልና ከዓለም አቀፍ ምንጮች ሲሆን የሚከተሉት የገንዘብ ምንጭ አማራጮች ወደፊት ይገመገማሉ።

17.1. ልዩ ልዩ የመንግሥት ታክሶችና ቀረጦች:

17.2. በመንግሥት ሠራተኞች መደበኛ መዋጮ ወይም የኢንሹራንስ ክፍያ:

17.3. የግሉ ዘርፍ ሠራተኞች ለጤና ፈንድ በሕጋዊ መንገድ የሚያደርጉት መዋጮ:

17.4. የግል ወይም የቡድን የጤና ኢንሹራንስ ክፍያ:

17.5. በመልካም ፈቃድ የሚደረጉ መዋጮዎች:

# HEALTH POLICY OF THE TRANSITIONAL GOVERNMENT OF ETHIOPIA

## PREAMBLE

Ethiopia, an ancient country with a rich diversity of peoples and cultures has however remained backward in socio-economic and political development, and in technological advances. Conventional health parameters such as infant and maternal mortality, morbidity and mortality from communicable diseases, malnutrition and average life expectancy place Ethiopia among the least privileged nations in the world. In recent times, the country has experienced severe manmade and natural calamities and political upheavals which have caused untold suffering to its peoples. At no time in the past has the country enjoyed the leadership of a representative government with a defined mandate and accountability.

In the field of health there was no enunciated policy up to the fifties. Subsequently, references to the development of health with provision of basic health services through a network of health centres and health stations and the need to give due attention to prevention alongside curative services could be discerned. Towards the end of the Imperial period a comprehensive Health Services Policy was adopted through initiatives from the World Health

Organization. However, the downfall of the regime precluded the possibility of putting this scheme to the test.

The Dergue regime that came into power in the midseventies formulated a more elaborate health policy that gave emphasis to disease prevention and control, priority to rural areas in health service and promotion of self-reliance and community involvement. But in practice the totalitarian political system lacked the commitment and leadership quality to address and maintain active popular participation in translating the formulated policy into action. In addition, the bulk of the national resources were committed to the pursuit of war throughout the life of the regime which left little for development activities in any sector.

Therefore,in health as in most other sectors, in both of the previous regimes there was no meeting ground between declaration of intent and demonstrable performance. Furthermore, the health administration apparatus contributed its own share to the perpetuation of backwardness in health development because, like the rest of the tightly centralized bureaucracy, it was unresponsive, self-serving and impervious to change.

The ***Health Policy of the Transitional Government*** is the result of a critical examination of the nature, magnitude and root causes of the prevailing health

problems of the country and awareness of newly emerging health problems. It is founded on commitment to democracy and the rights and powers of the people that derive from it and to decentralization as the most appropriate system of government for the full exercise of these rights and powers in our pluralistic society. It accords appropriate emphasis to the needs of the less-privileged rural population which constitute the over-whelming majority of the population and the major productive force of the nation. As enunciated in these articles, it proposes realistic goals and the means for attaining them based on the fundamental principles that health, constituting physical, mental and social well-being, is a prerequisite for the enjoyment of life and for optimal productivity. The Government therefore accords health a prominent place in its order of priorities and is committed to the attainment of these goals utilizing all accessible internal and external resources. In particular the Government fully appreciates the decisive role of popular participation and the development of self-reliance in these endeavours and is therefore determined to create the requisite social and political conditions conducive to their realization.

The Government believes that health policy cannot be considered in isolation from policies addressing population dynamics, food availability, acceptable living conditions

and other requisites essential for health improvement and shall therefore develop effective intersectorality for a comprehensive betterment of life.

In general,health development shall be seen not only in humanitarian terms but as an essential component of the package of social and economic development as well as being an instrument of social justice and equity.

Pursuant to the above the health policy of the Transitional Government shall incorporate the following basic components.

## GENERAL POLICY

1. Democratization and decentralization of the health service system.

2. Development of the preventive and promotive components of health care.

3. Development of an equitable and acceptable standard of health service system that will reach all segments of the population within the limits of resources.

4. Promoting and strengthening of intersectoral activities.

5. Promotion of attitudes and practices conducive to the strengthening of national self-reliance in health development by mobilizing and maximally utilizing internal and external resources.

6. Assurance of accessibility of health care for all segments of the population.

7. Working closely with neighbouring countries,regional and international organizations to share information and strengthen collaboration in all activities contributory to health development including the control of factors detrimental to health.

8. Development of appropriate capacity building based on assessed needs.

9. Provision of health care for the population on a scheme of payment according to ability with special assistance mechanisms for those who cannot afford to pay.

10. Promotion of the participation of the private sector and nongovernmental organizations in health care.

**PRIORITIES OF THE POLICY**

1. Information, Education and Communication (I.E.C.) of health shall be given appropriate prominence to enhance health awareness and to propagate the important concepts and practices of self-responsibility in health .

2. Emphasis shall be given to:-

   2.1 the control of communicable diseases, epidemics and diseases related to malnutrition and poor living conditions,

   2.2 the promotion of occupational health and safety,

   2.3 the development of environmental health,

   2.4 the rehabilitation of the health infrastructure and

   2.5 the development of an appropriate health service management system.

3. Appropriate support shall be given to the curative and rehabilitative components of health including mental health.

4. Due attention shall be given to the development of the beneficial aspects of Traditional Medicine including related research and its gradual integration into Modern Medicine.

5. Applied health research addressing the major health problems shall be emphasized.

6. Provision of essential medicines, medical supplies and equipment shall be strengthened.

7. Development of human resources with emphasis on expansion of the number of frontline and middle level health professionals with community based, task-oriented training shall be undertaken.

8. Special attention shall be given to the health needs of:-

   8.1 the family particularly women and children,

   8.2 those in the forefront of productivity,

   8.3 those hitherto most neglected regions and segments of the population including the majority of the rural population, pastoralists, the urban poor and national minorities,

   8.4 victims of man-made and natural disasters.

## GENERAL STRATEGIES

1. Democratization within the system shall be implemented by establishing health councils with strong community representation at all levels and health committees at grass-root levels to participate in identifying major health problems, budgeting, planning, implementation, monitoring and evaluating health activities.

2. Decentralization shall be realized through transfer of the major parts of decision-making, health care organization, capacity building, planning, implementation and monitoring to the regions with clear definition of roles.

3. Intersectoral collaboration shall be emphasized particularly in:

   3.1 Enriching the concept and intensifying the practice of family planning for optimal family health and planned population dynamics.

   3.2 Formulating and implementing an appropriate food and nutrition policy.

   3.3 Accelerating the provision of safe and adequate water for urban and rural populations.

3.4 Developing safe disposal of human, household, agricultural, and industrial wastes, and encouragement of recycling.

3.5 Developing measures to improve the quality of housing and work premises for health.

3.6 Participating in the development of community based facilities for the care of the physically and mentally disabled, the abandoned, street children and the aged.

3.7 Participating in the development of day-care centres in factories and enterprises, school health and nutrition programmes.

3.8 Undertakings in disaster management, agriculture, education, communication, transportation, expansion of employment opportunities and development of other social services.

3.9 Developing facilities for workers' health and safety in production sectors.

4. **Health Education** shall be strengthened generally and for specific target populations through the mass media, community leaders, religious and cultural leaders, professional associations, schools and other social organizations for:

4.1 Inculcating attitudes of responsibility for self-care in health and assurance of safe environment.

4.2 Encouraging the awareness and development of health promotive life-styles and attention to personal hygiene and healthy environment.

4.3 Enhancing awareness of common communicable and nutritional diseases and the means for their prevention.

4.4 Inculcating attitudes of participation in community health development.

4.5 Identifying and discouraging harmful traditional practices while encouraging their beneficial aspects.

4.6 Discouraging the acquisition of harmful habits such as cigarette smoking, alcohol consumption,drug abuse and irresponsible sexual behaviour.

4.7 Creating awareness in the population about the rational use of drugs.

5. **Promotive and Preventive activities shall address:**

5.1 Control of common endemic and epidemic communicable and nutritional diseases using appropriate general and specific measures.

5.2 Prevention of diseases related to affluence and ageing from emerging as major health problems.

5.3 Prevention of environmental pollution with hazardous chemical wastes.

6. **Human Resource Development shall focus on:**

6.1 Developing of the team approach to health care.

6.2 Training of community based task-oriented frontline and middle level health workers of appropriate professional standards; and recruitment and training of these categories at regional and local levels.

6.3 Training of trainers, managerial and supportive categories with appropriate orientation to the health service objectives.

6.4 Developing of appropriate continuing education for all categories of workers in the health sector.

6.5 Developing an attractive career structure, remuneration and incentives for all categories of workers within their respective systems of employment.

7. **Availability of Drugs, Supplies and Equipment** shall be assured by :

7.1 Preparing lists of essential and standard drugs and equipment for all levels of the health service system and continuously updating such lists.

7.2 Encouraging national production capability of drugs, vaccines, supplies and equipment by giving appropriate incentives to firms which are engaged in manufacture, research and development.

7.3 Developing a standardized and efficient system for procurement, distribution, storage and utilization of the products.

7.4 Developing quality control capability to assure efficacy and safety of products.

7.5 Developing maintenance and repair facilities for equipment.

8. **Traditional Medicine** shall be accorded appropriate attention by:

   8.1 Identifying and encouraging utilization of its beneficial aspects.

   8.2 Co-ordinating and encouraging research including its linkage with modern medicine.

   8.3 Developing appropriate regulation and registration for its practice.

9. **Health Systems Research** shall be given due emphasis by:

   9.1 Identifying priority areas for research in health.

   9.2 Expanding applied research on major health problems and health service systems.

   9.3 Strengthening the research capabilities of national institutions and scientists in collaboration with the responsible agencies.

   9.4 Developing appropriate measures to assure strict observance of ethical principles in research.

10. Family Health Services shall be promoted by:

10.1 Assuring adequate maternal health care and referral facilities for high risk pregnancies.

10.2 Intensifying family planning for the optimal health of the mother, child and family.

10.3 Inculcating principles of appropriate maternal nutrition.

10.4 Maintaining breast-feeding, and advocating home made preparation, production and availability of weaning foods at affordable prices.

10.5 Expanding and strengthening immunization services, optimisation of access and utilization.

10.6 Encouraging early utilization of available health care facilities for the management of common childhood diseases particularly diarrhoeal diseases and acute respiratory infections.

10.7 Addressing the special health problems and related needs of adolescents.

10.8 Encouraging paternal involvement in family health.

10.9 Identifying and discouraging harmful traditional practices while encouraging their beneficial aspects.

**11. Referral System shall be developed by:**

11.1 Optimizing utilization of health care facilities at all levels.

11.2 Improving accessibility of care according to need.

11.3 Assuring continuity and improved quality of care at all levels.

11.4 Rationalizing costs for health care seekers and providers for optimal utilization of health care facilities at all levels.

11.5 Strengthening the communication within the health care system.

**12. Diagnostic and Supportive Services for health care shall be developed by:**

12.1 Strengthening the scientific and technical bases of health care.

12.2 Facilitating prompt diagnosis and treatment.

12.3 Providing guidance in continuing care.

13. **Health Management Information system shall be** organized by:

13.1 Making the system appropriate and relevant for decision making, planning, implementing, monitoring and evaluation.

13.2 Maximizing the utilization of information at all levels.

13.3 Developing central and regional information documentation centres.

14. **Health Legislations** shall be revised by:

14.1 Up-dating existing public health laws and regulations.

14.2 Developing new rules and regulations to help in the implementation of the current policy and addressing new health issues.

14.3 Strengthening mechanisms for implementation of the health laws and regulations.

**15. Health Service Organization** shall be systematized and rationalized by:

15.1 Standardizing the human resource, physical facilities and operational systems of the health units at all levels.

15.2 Defining and instituting the catchment areas of health units and referral systems based on assessment of pertinent factors.

15.3 Regulating private health care and professional deployment by appropriate licensing.

**16. Administration and Management** of the health system shall be strengthened and made more effective and efficient by:

16.1 Restructuring and organizing at all levels in line with the present policy of decentralization and democratization of decision making and management.

16.2 Combining departments and services which are closely related and rationalizing the utilization of human and material resources.

16.3 Studying the possibility of designating under-secretaries to ensure continuity of service.

16.4 Creating management boards for national hospitals, institutions and organizations.

16.5 Allowing health institutions to utilize their income to improve their services.

16.6 Ensuring placement of appropriately qualified and motivated personnel at all levels.

17. Financing the Health Services shall be through public, private and international sources and the following options shall be considered and evaluated.

17.1 Raising taxes and revenues.

17.2 Formal contributions or insurance by public employees.

17.3 Legislative requirements of a contributory health fund for employees of the private sector.

17.4 Individual or group health insurance.

17.5 Voluntary contributions.